መልእክት ሁለት

**በመለኮታዊ ፍቅር ውስጥ በመኖር የመለኮታዊውን ሥላሴ መለኮታዊ እደላ መለማመድ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ኤፌ. 3፡14-19፤ መኃ. 1፡2-3፤ 3፡6፤ 4፡7፣ 15፤ 6፡4፤ 8፡6-7፤ ራእ. 19፡7፤ 21፡2

**I. መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ንጹህ እና እጅግ ቅዱስ በሆነ ስሜት የአጽናፍ አለም ጥንዶች የፍቅር ታሪክ ነው—እግዚአብሔር በክርስቶስ እንደ ሙሽራው እና በእግዚአብሔር የተቤዡት ህዝቡ እንደ ሙሽራይቱ— ዮሐ 3፡29፤ ማቴ. 25፡6፤ ራእ. 19፡7፤ 21፡2፤ 22፡17፡-**

ሀ. በየምእተ ዓመታቱ እግዚአብሔር ከሰው ጋር የፍቅር ፍላጎት ነበረው፤ አቻ ይኖረው ዘንድ በሆነው ዓላማው ሰውን ፈጠረው—ቁ. 17።

ለ. እግዚአብሔር አፍቃሪ ነው፣ ሰውንም እንደ አፍቃሪ በራሱ መልክ ፈጠረው፤ ይህም ማለት እርሱን ይወድደው ዘንድ ሰውን ፈጠረው ማለት ነው—ማር. 12፡30፤ ኤፌ. 3፡14-19።

ሐ. መላው መጽሐፍ ቅዱስ የመለኮታዊ ፍቅር ታሪክ ነው፣ መኃልየ መኃልይ የዚህ የፍቅር ታሪክ ምህጻር ነው—1፡2-3፤8፡14።

1. መጽሐፍ ቅዱስ የፍቅር መጽሐፍ ነው፣ ከጌታ ጋር ያለንም ግንኙነት እየጨመረ የሚመጣ የፍቅር ግንኙነት መሆን አለበት—መኃ. 4፡7።
2. በእኛ እና በጌታ መካከል ፍቅር ከሌለ እኛ አፍቃሪ ክርስቲያኖች ሳንሆን ሃይማኖተኛ ክርስቲያኖች ነን—1፡2-3።
3. በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ የመለኮታዊ ማጨት ቃል ነው፤ በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ፍቅራችንን እየፈለገ እንደሆነ እናያለን—2 ቆሮ. 11፡2።

መ. የእግዚአብሔርን የማጨት ቃል ከጠበቅን ለእርሱ ምላሽ የሚሰጥ፣ የጠበቀ ፍቅር ያስፈልገናል፤ እንዲህ አይነቱ ምላሽ የሚሰጥ ፍቅር በውዱ እና በአፍቃሪዋ መካከል ያለውን ፍቅር ስዕል በምናይበት በመኃልየ መኃልይ ተገልጿል—1፡2-4፤ 2 ቆሮ. 5፡14-15፤ ዮሐ 14፡21፣ 23፡-

1. የመኃልየ መኃልይ ርዕሰ ጉዳይ በላቀ ኃብቻ ውስጥ የአንድን አማኝ ከክርስቶስ ጋር እያደገ የሚሄድ የፍቅር ኅብረት ልምምድ የሚገልጥ የፍቅር ታሪክ ነው—1፡2።
2. መኃልየ መኃልይ፣ በክርስቶስ እንደ ሙሽራው እና በአፍቃሪዋ እንደ ሙሽራይቱ መካከል ያለውን የሙሽርነት ፍቅር በግጥም መልክ የሚያሳይ አስደናቂ እና ግልጽ ስዕል ነው—2፡4፤ 6፡3፣ 7፡11-12፤ 8፡5-6፣ 14።

**II. በመኃልየ መኃልይ መለኮታዊውን እደላ በመለማመድ እና በመለኮታዊው ፍቅር በመኖር መካከል ያለውን ግንኙነት እናያለን፡-**

ሀ. በእውነት ጌታን ከወደድን በእርግጥ በሕይወት ማደግ እና መለወጥ ይኖረናል—2 ቆሮ. 5፡14-15፤ 3፡18።

ለ. በመኃልየ መኃልይ ያለችው ፈላጊ ውዷን በጣም ስለምትወደው መለኮታዊ እደላን ትለማመዳለች፣ በሕይወት እድገቷም የማያቋርጥ ለውጥ አለ—1፡2-3፣ 4፣ 9፣ 12፣ 15፤ 2፡2፣ 14፤ 3፡6-7፤ 4፡7፣ 12-15፤ 6፡4፣ 10፣ 13።

ሐ. አንድ ሰው የሚወደው ነገር ላይ ሙሉ ልቡ፣ መላው ማንነቱም ሳይቀር በዚያ ነገር ላይ ይሆናል፣ ይያዛል እና ይወረሳል—1ጢሞ. 6፡10-11፤ 2 ጢሞ. 3፡2-4፤ 4፡8፣ 10፤ ቲቶ 1፡8፡-

1. “እግዚአብሔርን መውደድ ማለት መላው ማንነታችንን—ከልባችን፣ ከነፍሳችን፣ ከአእምሯችን እና ብርታታችን ጋር (ማር. 12፡30) መንፈሳችንን፣ ነፍሳችንን እና ሥጋችንን—ፈጽሞ በእርሱ ላይ ማድረግ፣ ማለትም፣ እርሱ ሁሉ ነገር ይሆንልን ዘንድ እና በተለይ በየዕለት ኑሯችን ከእርሱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ መላው ማንነታችን በእርሱ እንዲወረስ እና በእርሱ ውስጥ እንዲጠፋ መፍቀድ ነው (ከሪካቨሪው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም 1ቆሮ. 2፡9 የግርጌ ማስታወሻ 3)።
2. ጌታ ኢየሱስን መውደድ እርሱን ማድነቅ፣ ማንነታችንን ወደ እርሱ ማቅናት፣ ለእርሱ መከፈት፣ እርሱን መደሰት፣ የመጀመሪያውን ስፍራ ለእርሱ መስጠት፣ ከእርሱ ጋር አንድ መሆን፣ እርሱን መኖር እና እርሱን መሆን ነው—ማቴ. 26፡6-13፤ 2 ቆሮ. 3፡16፤ ማር. 12፡30፤ ቆላ. 1፡18፤ 1 ቆሮ. 6፡17፤ ፊሊ. 1፡20-21፤ ከእንግሊዝኛ የመዝሙር መጽሐፍ ቁጥር 477፣ ስንኝ 2።

**III. ቴርሳ እና ኢየሩሳሌም ጥበቃው ለመሆን ዙሪያውን ከከበበው ከእግዚአብሔር ከተማ ጋር የእግዚአብሔርን ማደሪያ፣ የእግዚአብሔርን መኖሪያ ስፍራ በምሳሌ ያሳያሉ—መኃ. 6፡4፡-**

ሀ. የክርስቶስ አፍቃሪ የእግዚአብሔር ማደሪያ ለመሆን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ስትሆን በእግዚአብሔር ዓይን እርሷ እንደ ቴርሳ ውብ እንደ ኢየሩሳሌም ያማረች ናት።

ለ. በክርስቶስ ትንሣኤ በእርገት በመኖሯ አማካኝነት የእግዚአብሔር ህንጻ፣ የእግዚአብሔር ማደሪያ እና ጥበቃ ለመሆን የክርስቶስ አፍቃሪ በክርስቶስ ሕይወት ብልጥግናዎች ትበስላለች—ተዛ. ዘፍ. 2፡8-12፣ 18-24፤ 1 ቆሮ. 3፡9-12።

ሐ. የክርስቶስ አፍቃሪ፣ ከትንሣኤው ልምምዷ በኋላ በመስቀሉ በኩል የክርስቶስን እርገት በመለማመድ በቅድስተ ቅዱሳን፣ በሰማያዊው መቅደስ ውስጠኛው ክፍል፣ በመጋረጃው ውስጥ ትኖራለች—መኃ. 4:8፡፡

መ. ጌታን በምርጡ ፍቅር በመውደድ የእርሱ መኖሪያ ስፍራ ለመሆን ወደ ሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ተካትተናል—ራእ. 2:4፤ ዮሐ 14:20-21፣ 23፤ ኤፌ. 3:17፦

1. ከእኛ ጋር አንድ ለመሆን፣ ለመዋሐድ እና ከእኛ ጋር ለመካተት ለእግዚአብሔር ናፍቆት የሚሰጠው በእርሱ ውስጥ ያለው ፍቅር ነው፣ እኛም አንድ እንድንሆን፣ እንድንዋሐድ እና እንድንካተት ናፍቆት የሚሰጠን ያው አንዱ ፍቅር ነው—1 ዮሐ 4:19፣ 8፣ 16።
2. ጌታን በምርጡ ፍቅር በመውደድ እና በመለኮት ፍቅር ውስጥ በሁሉም ገጽታዎች በመሳተፍ እንደ የቅድስተ ቅዱሳኑ መተለቅ አዲሲቱን ኢየሩሳሌም እንሆናለን—መኃ. 1:2-3፤ 2:14፤ 4:8፤ 6:4፤ ራእ. 21:9-10።

ሠ. የእግዚአብሔር መቅደስ መሆን ፍለጋ ከሌለው ከክርስቶስ ሕይወት ብልጥግና ጋር በክርስቶስ ሕይወት እስከንበስል ድረስ መገንባት ነው (ከክርስቶስ አካል መገንባት ጋር ይገናኛል) —ኤፌ. 4:12-16፦

1. በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ግንባታ በቴርሳ እና በኢየሩሳሌም እንደ ምሳሌ ታይቷል፤ በአዲስ ኪዳን ይህ ሕይወታዊው የክርስቶስ አካል ነው—ኤፌ. 4:16
2. የአካሉ መገንባት ሕይወታዊ ነው፣ በሕይወት በማደጋችን እና በመብሰላችን ላይም ይመሠረታል—ቁ. 15።
3. በመጨረሻም ይህች የክርስቶስ ሚስት የሆነችው (5:25-32) የክርስቶስ አካል ሕይወታዊ ግንባታ፣ ለዘላለም እንደምትኖረው እንደ የእግዚአብሔር እና በእርሱ የተዋጁት የጋራ መኖሪያ ስፍራ፣ እንደ ቅድስተ ቅዱሳኑ መጠናቀቅ ቅዲስቲቱን ከተማ፣ አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ያጠናቅቃል—ራእ. 21:2-3፣ 16፣ 22።

## IV. በክርስቶስ ሕይወት በመብሰል ሊጋብቻቸው እርሱን ለመመጠን የክርስቶስ ርቢ እና ብዜት መሆኗን በማሳየት የክርስቶስ አፍቃሪ ሱላማጢስ ሆናለች—መኃ. 6:13፦

ሀ. የእግዚአብሔር ውጥን ራሱን ከእኛ ጋር እና እኛን ከራሱ ጋር—ተመላኪነቱን ሳይጨምር በሕይወት እና በባሕርይ አንድ ማድረግ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ይነግረናል—ራእ. 21:2፤ 22:17።

ለ. የመለኮታዊ መገለጥ ከፍተኛ ጫፍ ላይ—እግዚአብሔር ሰው ሆነ ሰው በሕይውት እና በባሕርይ እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ—እንዴት እንደምንደርስ ስናስብ ራሳችንን መታመን የለብንም፣ ነገር ግን የምሕረት፣ የክብር እና የምስጋና ዕቃዎች እንዲያደርገን እንደ ፍቅር፣ እንደ ኃይል፣ እና እንደ ምሕረት በጌታ ላይ መደገፍ አለብን—መኃ. 8:5-6።

© 2022 Living Stream Ministry